በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

# *ሮማ ካቶሊክና የምስራቅ ኦርቶዶክሳውያን*

# ክፍል አራት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

መጋቢት ፱ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

## የሮማ ካቶሊክ #ቤተክርስቲያን;

- ኢየሩሳሌም በ70 ዓ. ም. በጥጦስ ከወደመች በኋላ በኢየሩሳሌም የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ለጊዜውም ቢሆን ተዳክመው ነበር፡፡ በዚህም አጋጣሚ የሮም ጳጳሳትና አስተዳደርም ወደ ኢየሩሳሌም ለመስፋፋት ዕድል አገኙ፡፡

- በየጊዜው የተፈጠሩ ፓለቲካዊ ሁኔታዎች የሮም ጳጳሳትና ፓፑ በዓለም የተለያዩ ክፍሎች ተፅዕኖ ማሳደር እንዲችሉና በዚህም እንዲቀጥሉ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

- ከአራተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመንም በቢዛንታየን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ሁሉ ተቆጣጠሩ፡፡ የሮምም ጳጳሳት በዓለም ያሉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጠበቆች አድርገው ራሳቸውን ቆጠሩ፡፡ #ሮም የቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ስለሆነች የሮሙ ፓፕ የሁሉም ራስ ከተማዋም የክርስቲያኖች ማዕከል ናት; ብለው ማወጅ ጀመሩ፡፡

- እያደርም #ያለ ሮማ ማንኛውም ሃይማኖታዊ ውሳኔ ተቀባይነት አይኖረውም; አሉ፡፡ አያይዘውም በ451 ዓ.ም. ምስራቃውያን መለካውያንን ይዘው የንስጥሮስን ትምህርት በማሻሻል ንጉሳቸው መርቅያንን ለማስደሰት ጥንታውያኑን አብያተ ክርስቲያናት በማግለል ለብቻቸው በኬልቄዶን ጉባኤ አድርገው #ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው; ብለው ውሳኔ ወሰኑ፡፡ ይህም በዮሐ. 10፡30 ከተጻፈው ጋር ይጋጫል፡፡

# የሮማ ካቶሊክ #ቤተክርስቲያን;

- አንዲቱንም ቤተክርስቲያን ትተው ለብቻቸው ምስራቃውያን ኦርቶዶክስን (ግሪክ፤ ሩሲያ፤…) አስከትለው ወጡ፡፡ እነዚህም የምድራዊውን ንጉሥ ፈቃድ ለመፈጸም በሥጋ ሀሳባቸው ተጉዘዋልና ጉባኤያቸው #ጉባኤ ከለባት; እነርሱም #መለካውያን; ይባላሉ፡፡

- በዚህ ጉባኤ ቀዳምያኑ ኦርየንታል ኦርቶዶክሶች (ግብጽ፤ ሶርያ፤ ሕንድ፤ አርመን፤ ኢትዮጵያ) አልተሳተፉም፡፡ መለካውያኑ አባቶታችንን አስገድደው የውሳኔያቸውን አሳብ እንዲቀበሉ ለማድረግ ሞክረው ነበር፡፡ የግብጹ ፓትርያርክ እንደነበረው እንደ ዲዮስቆሮስ ያሉት ግን ጥርሳቸውን በመነቀል፤ ጽሕማቸውንም በመነጨት አንዲቱን፤ ሐዋርያዊቱን፤ ቅድስቲቱንና ዓለም አቀፋዊቱን ቤተክርስቲያን በምድራውያን ነገሥታት ሐሳብና ፈቃድ ሳትበረዝ ትምህርቷና ትውፊቷ ተጠብቆ እንዲኖር አድርገዋል፡፡

- #*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ፡፡*; ትን ኤር 6 ፡ 16፡፡

- በሰባተኛውም መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የሮሙ ፓፓ አራፎን አልተቀበሉትም እንጂ #የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ነንና ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የሮማን አለቅነት ወይም ራስነት; እንዲቀበሉ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በስምንተኛውም መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ፖፕ ስቴፋን #እኔ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ነኝ … በእግዚብሔር ፈቃድ የዓለም ብርሃን ሆኜ ተልኬላችኋለሁ…; ብሎ ነበር፡፡

# የሮማ ካቶሊክና ምስራቃውያን ኦርቶዶክሶች

- እስካሁን ያየነው የሮማውያን እንቅስቃሴ ቢኖርም ምስራቃውያኑ ከሮም ካቶሊክ ሳይለዩ በሁሉም እየተባበሩ ሞቆየታቸውን ነው። በዚህም ሁኔታ እስከ 1054 ዓ.ም. ድረስ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ በ1054 ዓ.ም. ተለያዩ። ለመለያየታቸውም ምክንያቶቹ የሮማ ካቶሊክ የጨመረቻቸው እንግዳ ትምህርቶች ናቸው ይላሉ። እነዚህም እንግዳ ትምህርቶች፡-
    1. በጸሎተ ሃይማኖት ላይ መንፈስቅዱስን ከአብና ከወልድ የሠረጸ ነው። ዮሐ. 15፡26
    2. የሮም ፖፕ አይሳሳትም የሁሉም አለቃ ወይም ራስ ነው።
    3. ድንግል ማርያም ከአርያም የመጣች ናት። ነገር ግን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘር የተቆጠረለት በእመቤታችን የተነሳ እንደሆነ ልብ እንበል። ማቴ 1፡1

- #የሮም ፖፕ አይሳሳትም የሁሉም አለቃ ወይም ራስ ነው; በማለት ለሚያነሱት የሚያቀርቡት ምክንያት በማቴ 16፡18 #አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥; በማለት የተነገረውን ነው። ትርጉሙም ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጠው ምላሽ እንደተገለጠው ቤተክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነት ላይ ትታነጻለች ማለት ቢሆንም እነርሱ ግን በራሱ በጴጥሮስ ላይ አጥንቱ ተከስክሶ ደሙ ፈሶ ማለት አለመሆኑን ካለመገንዘባቸው በላይ ለሚሉትም በቂ ማገናዘቢያ ምንጭ የላቸውም።

# የሮማ ካቶሊክና ምስራቃውያን ኦርቶዶክሶች

- ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን አለቃቸው አድርገው አልሾሙትም፡፡ በ51 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም በተደረገውም የሐዋርያት የመጀመሪያ ሲኖዶስ ሰብሳቢው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ነበር፡፡ የሐ. ሥራ 15 ፡ 1 — 41፡፡

- የቅዱስ ጴጥሮስን ሥልጣን በተመለከተ እጁን በመጫን አገልግሎቱን የፈጸመው በሮም ብቻ ሳይሆን በእስክንድርያ፤ በአንጾኪያና በሌሎችም ጭምር ነበር፡፡ ሮማውያን ራሳቸውን ቁልቁል ከሰቀሉት ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በማገናኘት ራሳቸውን የበላይ አድርገው የቆጠሩት ለሥልጣን ከነበራቸው ጥማትና ከአንዲቱም ቤተክርስቲያን አስቀድመው ከመለየታቸው የተነሳ ነው፡፡ ይህም ትምህርት በአንዲቱ ቤተክርስቲያን አስቀድሞ ያልነበረ እንግዳ ትምህርት ነው፡፡

- የጴጥሮስ ምትክ ነው አይሳሳትም የሚሉትንም በተመለከተ እንኳን ምትክ የሆነው ራሱ ጴጥሮስ እንኳ በጌታችን ከደካማ ሐሳቡ የተነሳ በጌታችን የተገሰጸ፤ ቃሉንም ለመጠበቅ አለመቻሉንም መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል፡፡ ማቴ 16፡23፡፡ ማቴ 26፡34-35፤ ማቴ 26፡69-75፡፡ እግዚአብሔር ካላገዘው በቀር በእግአብሔር ፊት እንኳን አርአያው ወደ ጥፋት የሚመራው ሰው፤ ሰማያትም ንጹሐን አይደሉም፡፡ ኢዮብ 15፡15

- ይህ የመለካውያን የተሳሳተ ከሥልጣን፤ ከጥቅም ጋር የተቆራኘ አካሄድ ለሉተር መነሳት ምክንያት ሆኗል፡፡

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሮማ ካቶሊክ ልዩነት

በሮማ ካቶሊክ ከትውፊተ ቤ/ክ የወጣ የተሳሳተ መንገድ የተነሳ የምንለያይባቸው የእምነት መሠረቶች ወይም ትምህርቶች

1. የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት
2. የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክነት
3. የፖፕ አለመሳሳት
4. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም
5. ቅዱስ ጴጥሮስ
6. የተሳሳተ ትውፊት
7. ጾም

## ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

1. ሁሉም የቤተክርስቲያን ምስጢራት የሚፈጸሙት በቆሳትና በቀሳውስት ብቻ ነው።
2. ሥጋውን የሚያቀብለው ቄሱ ሲሆን በዕለት የተሰዋው መሥዋዕት አያድርም። ዘጸአት 12፡10
3. ምስጢረ ሜሮን ከጥምቀት ቀጥሎ ወዲያው ይፈጸማል።
4. ቤ/ክ ትውፊታዊትና መጽሐፍ ቅዱሳዊት ናት።
5. ኦርቶዶክሳውያን መጋባት የሚችሉት ከኦርቶደክሳውያን ጋር ብቻ ነው። ነህምያ 13፡27
6. በዝሙት ከሆነ ምክንያት በቀር መፍታት አልተፈቀደም። ማቴ 5፡32።
7. ቅዳሴዋ ከጥንት እንደነበረው በዓለሙ ሁሉ ተጠብቆ ይኖራል።
8. በቀን ከአንድ ጊዜ በላይ በመንበሯ አይቀደስም።

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የሮማ ካቶሊክ ልዩነት

## በሮማ ካቶሊክ

1. ጥምቀት፤ ተክሊልና ቅዱስ ቁርባን በዲያቆናት ይፈጸማሉ። ሌሎቹ ምስጢራት ግን በቀሳውስትና በካርዲናሎች ይፈጸማሉ (ቀንዲል፤ ንስሐ፤ ክህነትና ሜሮን)። ይህም ትውፊተ ቤ/ክ አይደለም።
2. ሥጋውና ደሙን የሚቀበሉት ቀሳውስት ብቻ ናቸው። ምዕመናኑን ግን ሥጋውን ብቻ ያቆርቧቸዋል። ይህም ከዮሐ 6፡54 ጋር ይለያያል።
3. መሥዋዕቱን አዘጋጅተው እያስቀመጡ - እያዋሉና እያሳደሩ ያቀብላሉ። ይህም ትውፊተ ቤ/ክ አይደለም።
4. ካቶሊካዊ ካቶሊካዊ ያልሆኑትን ሊያገቡ ይችላሉ።
5. ፍቺ በዝሙትም የተነሳ ቢሆን ፈጽሞ አይፈቀድም። ማቴ 5፡32 ግን በዝሙት ከሆነ ... ይላል።
6. ቁርባኑን ለወንዱም ለሴቱም እንዲያቆርቡ ይሰጣሉ። ወንድም ሴትም ያቀብላሉ።
7. በአንድ መንበር ከአንድ ጊዜ በላይ ይቀድሳሉ።
8. በልተው ጠጥተው ይቀድሳሉ፤ ይቆርባሉ፤ ያቆርባሉ።
9. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የሠረጸ ነው ይላሉ። ዮሐ 15፡26 ይህን አይልም።
10. ድንግል ማርያም አባትና እናት የላትም። መጽሐፍም ትውፊትም አይልም።
11. ፖፑ አይሳሳትም፤ ሮም የክርስትና ማዕከል ናት፤ ቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ ነው። መጽሐፍም ትውፊትም አይልም። ነገር ግን ማቴ 16፡23። ማቴ 26፡34-35፤ ማቴ 26፡69- 75። የሐ. ሥራ 15፡9። አይሉም።
12. በጾም ወተት መጠጣት... ይቻላል። በትውፊትም በመጽሐፍም አልተፈቀደም። ሕዝ 4፡1-ፍጻሜ

ይቀጥላል

… ሌሎችስ?

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡